መጋቢት 14/2004 ዓ.ም.

# በደቡብ ኢትዮጵያ ስምንት የመኢአድ አባላት የዘጠኝ ወር እስራት ተፈረደባቸው፡፡

በደቡብ ኢትዮጵያ በጎፋ ልዩ ዞን በደንባ ጎፋ ወረዳ የሚኖሩ ስምንት የወረዳው የመኢአድ አባላት መጋቢት 14/2004 ዓ.ም .በደምባ ጎፋ ፍርድ ቤት የግለሰብ ማሳ አንቆፍርም በሚል ወንጀል ተከሰው መቅረባቸው ይታወቃል፡፡ አቶ አብርሃም አዳኝ የተባሉ ዳኛ የዘጠኝ የዘጠኝ ወር እስራት የፈረዱባቸው መሆኑን አቶእንድርያስ ኤሮ የመኢድ የማዕከላዊ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባልና የፓርቲው የደቡብ ቀጠና ኃላፊ ለመኢአድ የህዝብ ግንኙት ቋሚ ኮሚቴ ገለጹ፡፡

የዘጠኝ ወር እስራት ከተፈረደባቸው ስምንት የመኢአድ አባላት ስድስቱ የደንባ ጎፋ ወረዳ የዘንጋ አይንዴ ቀበሌ የመኢአድ ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ናቸው፡፡ ስምንቱ አባላት

1ኛ, አቶኢልካዬ ኢሮ ፣ 2ኛ, ሃምሳ አለቃ ማናዬ ዋለልኝ፣ 3ኛ, አቶ መኮንን ዳና፣ 4ኛ, አቶ መንግስቱ ማናዬ፣ 5ኛ, ቡኩሎ ፈለአ፣ 6ኛ, አቶ ሴባሮ ሼናሞ፣ 7ኛ, አቶ ጉዤጉቼ እና 8ኛ, አቶ እንዳለ ኤሮ ሲሆኑ አቶ ኢልካዬ ኤሮ እና አቶ እንዳለ ኤሮ የአቶ እንድርያስ ኤሮ ወንድሞች መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ሁለት የመኢአድ ተከሳሾች አበና አሊሶ እና ሙጉቴ ሙኩሉ ብር ሶስት መቶ ሦስት ሦስት መቶ የተቀጡ መሆናቸው ታውቋል ፡፡

ከዚህም በተጨማሪ ሰኞ መጋቢት 17/2004 ዓ.ም ከደምባ ጎፋ ወረዳ 6 ሰዎች የፍርድ ቤት ቀጠሮ ያለቸው ሲሆን ሌሎች 6 ሰዎች ደግሞ፣ ከደንባ ቀበሌ ለየካቲት 26/2004 ዓ.ም እና የወይዳ ያለው ቀበሌ 4 ሰዎች እንዲሁ ለመጋቢት 26/2004 ዓ.ም. የፍርድ ቤት ቀጠሮ ያላቸው መሆኑንም አቶ እንድርያስ ኤሮ ገልጸዋል፡፡